# የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ኅብረት (ኢዴኃኅ)
# UNITED ETHIOPIAN DEMOCRATIC FORCES (UEDF)

## ከኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ኅብረት የተሰጠ ልዩ መግለጫ

### ግንቦት ሰባት- የአንድነት በግለጫ ዳግም አድዋን የአንድነታችን እንጅ የልዩነት ቀን አናድርጋት!

የኢትዮጵያ ሕዝብ ለልዩ ልዩ የግፍ አገዛዞችና ለቀጣይ መከራ ዙር ተዳርጎ የኖረው የሚፈልገውን አስተዳደር ለመወሰን የሥልጣኑ ባለቤት መሆን ባለመቻሉ ነው:: በውድ አገራችን ኢትዮጵያ ሰላማዊ የሥልጣን ሽግግር አለመኖርና ገዥዎች በአመፅ ላይ የተመሠረተ ዝውውር በመኻላቸው መቀጠላቸው ሕዝቡ የራሱ ዕድል ወሳኝ እንዳይሆንና ለማያባራ ስቃይ ብቻ እንደተፈጠረ ሁሉ በችግርና በድኅነት እንዲኖር ሆኗል::

የኢትዮጵያ ሕዝብ ረዥም ውጣ ውረድ በበዛበት ታሪኩ ለመጀመሪያ ጊዜ የሥልጣኑ ባለቤት ለመሆን የሚያስችል ታላቅ ድል ግንቦት ሰባት ቀን ፲፺ ዓ/ም ተቀዳጅቷል:: ሕዝባችን ባደረገው መራር ትግል መከፋፈልን አስወግዶ ዳግም ዓድዋን በደሙና በላቡ አስገመዝግቧል:: ግንቦት ሰባት የኢትዮጵያ ሕዝብ ቁርና ሐሩርን፥ ረሃብና ጥማትን፥ ጉቦና ማስፈራራትን፥ ችግርና እንግልትን ሁሉ ተቋቁሞ የፖለቲካ ብስለቱን፥ ጨዋነቱን፥ አስተዋይነቱን፥ መንፈሰ ጠንካራነቱን፥ ቆራጥነቱንና ለለውጥ ዝግጁነቱን ያስመሰከረበት፤ አምባ-ገነን አገዛዝን፥ ኋላ-ቀር መከፋፈልን፥ በአመፅና በጉልበት ላይ የተመሠረተ የገዥዎች የሥልጣን ቅይይርን ወደ መቃብር የወረወረበት፤ አንድነትን፥ መቻቻልን፥ አዲስ ተስፋንና ዴሞክራሲን ያነገሰበት ከትውልድ ትውልድ በታሪክ ሲዘከር የሚኖር ታላቅ የድል ቀን ነው:: በዚች ታሪካዊ ቀን የኢትዮጵያ ሕዝብ በሰላማዊ መንገድ መንግሥት መቀየር ብቻ ሳይሆን ኋላ-ቀር የአመፅ ሥርዓት አዙሪትም መስበር እንደሚችል አረጋግጧል::

ይሁንናም ለሕዝብ ምንም ዓይነት ከበሬታ የሌላቸውና አርቆ ማየት የተሳናቸው የኢሕአዴግ አሸባሪ አምባ-ገነን መሪዎች ይኸንን የሕዝብ ድል በፀጋ ከመቀበልና ለጋራ እድገት በመሥራት ፋንታ በጉልበት ሥልጣን የሙጥኝ በማለት ድምፁን የነፈገው ሕዝብ ላይ የበቀል ጦርነት አውጀው እያሰቃዩት ይገኛል:: የሕዝብ ድምፅ ይከበር ብለው ጥያቄአቸውን በሰላማዊና በሕጋዊ መንገድ የጠየቁ ንፁህ ዜጎችን በጭካኔ ጨፍጭፎ፥ በብዙ ሽህ የሚቆጠሩትን በግፍና በገፍ በየማጎሪያ ጣቢያው አምቆ፥ ሕዝብ አመኔታውን ጥሎባቸው እንዲመሩት የመረጣቸውን የድርጅት መሪዎች፥ የነፃው ኅትመት ክፍል ወገኖችን፥ በምግባረ-ሰናይ ተግባር ላይ የተሰማሩትንና የሰብኣዊ መብት ተሟጋቾችን በሕገ-ወጥ መንገድ አስሮ፥ የሕዝባችን መሠረታዊ መብቶቹ ሳይቀር በጅምላ ገፎ እያሰቃየ ይገኛል:: እነሆ የኢትዮጵያ ሕዝብ በግንቦት ያስመዘገባቸውን ድሎች ላለማስነጠቅ ከአሸባሪው የአቶ መለስ አምባ-ገነን አገዛዝ ጋር ዓመቱን ሙሉ የሚያደርገውን መተናነቅ ቀጥሎበታል:: መቸም አምባ-ገነኖች ከታሪክ አይማሩም እንጅ ምንም ያህል ግፍ፥ ምንም ያህል ኃይል መጠቀም አንድ ሕዝብ በቁርጠኝነት የተነሳበትን ዓላማ ምናልባት የቀን ጉዳይ እንጅ ጨርሶ ማስቆምም ሆነ አፍኖ ሊያስቀር አይችልም::

የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ኅብረት ሕዝባችን ያስመዘገባቸውን የግንቦት ድሎች እንዳይቀለበሱ በሁሉም ዘርፍ የሚያደርገውን አኩሪ ተጋድሎ እያደነቀ፥ ጊዜው


ዋና መሥሪያ ቤት (Main Office)
ፖ.ሣ.ቁ./P.O.Box 73246
Washington, D.C. 20056-3246,U.S.A
ስልክ/Tel.: 202-291-4217;
ፋክስ/Fax: 202-291-7645

ኢትዮጵያ (Ethiopia)
ፖ.ሣ.ቁ./P.O.Box
Addis Abeba,Ethiopia
ስልክ/(Tel.) 251_______
ፋክስ/Fax:2511________

አውሮጳ (Europe)
Jonathan Str. 82
2524 JJ The Hague,
Netherlands
Tel/Fax 31 70 394 6132

የሚጠይቀው የግል አጀንዳ ማራመድንም ሆነ የተናጠል እንቅስቃሴን ሳይሆን ትብብርን ስለሆነ፥ ኅብረታችን ከምሥረታው ጀምሮ በያዘው ሁሉን ያስተባበረ አካሄድ መተክላዊ አቋሙ መሠረት የሕዝባችንን ፍላጎት፥ ተጋድሎና መስዋዕትነት የሚመጥን አፋጣኝ ምላሽ ለመስጠት ይቻል ዘንድ የተቃዋሚው ክፍል ሰፊና ትርጉም ያለው ትብብር በአስቸኳይ እንዲመሠረት በዚህ አጋጣሚ ጥሪውን በድጋሜ ያቀርባል።

እንደሚታወቀው በዓለም ዙሪያ ያሉ ኢትዮጵያውያን በዚች የኢትዮጵያ ሕዝብ ፍላጎቱን በአንድነት በገለጸባት ታሪካዊ ቀን ለሕዝብ ድምፅ መከበር ሲሉ ሕይዎታቸውን ያጡ ሰማዕታትን ለመዘከር፥ በአምባ-ገነኖች እስር ቤቶችና ማጎሪያ ጣቢያዎች እየተሰቃዩ ያሉ ዜጎቻችንን ለማሰብና ለማክበር፥ የኢትዮጵያ ሕዝብ በአልሞት ባይ ተጋዳይነት ከአሸባሪ አምባ-ገነኖች ጋር የሚያደርገውን ትግል ለማድነቅና የትግል አጋርነታችንን ለመግለጽ በመጭው ግንቦት ፯ ቀን ፲፱፻፺፰ ዓ.ም. በልዩ ልዩ የዓለም ክፍሎች ሰላማዊ ሰልፎችና ሌሎች ዝግጅቶች እየተደረጉ ነው። እነዚህ እቅዶች ተግባራዊ እንዲሆኑ ኅብረቱ ከቅንጅትና ከሌሎች አገር-ወዳድና ዴሞክራሲያዊ ወገኖች ጋር ጥረት በማድረግ ላይ ይገኛል። ይኽን በተመለከተ በዋሽንግተን የሚገኘው የቅንጅት የድጋፍ ሰጭ አካል በሌላው የዓለም ክፍል ሁሉ በዚህ ቀን በጋራ ከሚደረገው በተለየ ለብቻው በግንቦት ስምንት ሰላማዊ ሰልፍ ጠርቷል። ዋሽንግተን ብቻ በቅንጅቱ ስም ለብቻ ተለይቶ በግንቦት ስምንት ሰላማዊ ሰልፍ ለማድረግ በመወሰኑ ሃዘኔታችንንና ቅሬታችንን ገልጸናል። እንደሌላው ቦታ ሁሉ በዋሽንግተንም በግንቦት ሰባት እንዲካሄድ የተቃደውን ሰላማዊ ሰልፍ ቅንጅቱ አብሮ እንዲያዘጋጅና የኢትዮጵያ ሕዝብ አንድነቱን ያረጋገጠበትን ታሪካዊ ቀን በአንድ ላይ ለማክበር እንዲቻል ጥሪ ቀርቧል፥ ውይይት ተካሄዷል። በአንድ ከተማም ሁለት የተለያዩ ሰላማዊ ሰልፎች እንዳይደረጉ ጥረት ተደርጓል። ሆኖም ዋሽንግተን ያለው የቅንጅት ድጋፍ ሰጭ አካል ግንቦት ሰባትን ወያኔ/ኢሕአዴግ ስለሚያከብር የኢትዮጵያ ሕዝብ ድል ያስመዘገበበትን ቀን ሳይሆን ኢሕአዴግ ሥልጣን የቀማበትን ቀን ነው የማስበው በማለት በግንቦት ስምንት የጠራውን ሰልፍ ለመለወጥ ፍላጎት እንደሌለው ገልጿል።

የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ኅብረት በሌሎች የዓለም ክፍሎች እያደረገ እንዳለው ሁሉ ዋሽንግተንም ከሌሎች ወገኖች ጋር በግንቦት ሰባት ሰላማዊ ሰልፍ የጠራና የተዘጋጀ ቢሆንም ለሕዝብ ባለው አክብሮት፥ ሕዝብ አንድነቱን ባረጋገጠበት ቀን ወገናችን በአንድ ከተማ ለአንድ ዓላማ ሁለት ቀን ሰላማዊ ሰልፍ እንዲወጣ በማድረግ ክፍፍል እንዳይኖር በማሰብ፥ ሕዝብንም ላለማሳዘንና መከፋፈል ከእምነታች ውጭ ስለሆነ በግንቦት ሰባት ቀን ፲፱፻፺፰ ዓ/ም በዋሽንግተን ለማድረግ ያቀደውን ሲላማዊ ሰልፍ በተባበሩት መንግሥታት መቀመጫ ኒው ዮርክ ከተማ እንዲደረግ መወሰኑን በአክብሮት ይገልጻል። እንዲህ ዓይነት የተለያየ አካሄድ እንዲቀጥል መፍቀዱ የሕዝባችንን የጋራ ትግል ስለሚጎዳ ትምህርት ሊሰጥ እንዲችል ወደፊት ማብራሪያ ይሰጥበታል።

ድል ለኢትዮጵያ ሕዝብ!
አንድነት ኃይል ነው!!

የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ኅብረት (ኢዴኃኅ)
ሚያዝያ ፳፬ ቀን ፲፱፻፺፰ ዓ/ም